2023



### የወላጅ ተከታታይ መረጃ

በ Maryland የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች፦

# የልዩ ፍላጎት ትምህ ርት ሂደት

**የልዩ ፍላጎት ትምህርት ሂደት** | የወላጅ መብቶች | IEPን መረዳት | የሁለተኛ ደረጃ ሽግግር



# መግቢያ

**በ Maryland የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት የወላጅ መመሪያ፤ የ Maryland ከልደት እስከ 21 የወላጅ ተከታታይ መረጃ ክፍል ሲሆን፤** በሜሪላንድ የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት ስርዓት ውስጥ ቤተሰቦችን ለመደገፍ የተነደፈ የሕትመት ስብስብ ነው። በዚህ ቡክሌት፣ ወደ ቁርጠኛ ባለሙያዎች ማህበረሰብ እንኳን ደህና መጡ ልንልዎት፣ እና የልጅዎን ስኬት ለመደገፍ እና ቤተሰብዎን ለመርዳት በፌደራል እና በስቴት ህግ በተፈጠረው ሂደት ውስጥ ልንመራዎ እንፈልጋለን።



# የማውጫ ሰንጠረዥ

ገጽ 4
**የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች**

ገጽ 5
**የልዩ ፍላጎት ትምህርት ምንድን ነው?**

ገጽ 6
**የ Maryland IEP ሂደት**

ገጽ 11
**ለወላጆች የማረጋገጫ ዝርዝር**

ገጽ 13
**ጥያቄዎች ካሉኝ ወይም እርዳታ ቢያስፈልገኝስ?**

ለበለጠ መረጃ በዚህ ይጎብኙን
**www.marylandpublicschools.org**

# ወደ **Maryland የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች** እንኳን ደህና መጡ

**ወላጆች በልጆቻቸው ትምህርት ውስጥ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ።** ይህ በተለይ አካል ጉዳተኛ የሆኑ ልጆች ላሏቸው ወላጆች እውነት ነው። ልጅዎ ምን በማድረግ እንደሚደሰት እና በምን እንደሚቸገር ያውቃሉ። ልጅዎ በሚቀጥለው ዓመት ምን እንደሚያከናውን እና ትምህርቱን ሲጨርስ ምን እንደሚያደርግ ራዕይ አለዎት።

ልጅዎ አካል ጉዳተኛ ሲሆን እና የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት የሚፈልግ ከሆነ ስለ ልዩ ፍላጎት ትምህርት ሂደት ማወቅዎ አስፈላጊ ነው። የልጅዎ ምርጥ ተሟጋች እርስዎ ነዎት። የልዩ ፍላጎት ትምህርት ሂደቱን መረዳትዎ፣ ከልጅዎ የግለሰባዊ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን ጋር ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመስራት ይረዳዎታል። ይህ ደግሞ ልጅዎ በትምህርት ቤትም ሆነ ከዚያ ውጪ ስኬታማ እንዲሆን ይረዳዋል። እርስዎ ስለ ልጅዎ ትምህርት ውሳኔዎችን የሚያሳልፈው ቡድን አካል ነዎት። እርስዎ የልጅዎ ቡድን የሚያስፈልገው እውቀት እና ችሎታ አለዎት።

ይህ ቡክሌት በ Maryland ውስጥ ስላለው የልዩ ፍላጎት ትምህርት ሂደት አጠቃላይ እይታ ይሰጣል። በተጨማሪም በሂደቱ ውስጥ ያለዎትን ሚና ለመረዳት እና ለስብሰባዎችዎ እንዴት እንደሚዘጋጁ ጠቃሚ ምክሮችን ይሰጥዎታል።

# ሕጉ ምን **ይላል**

## IDEA ምንድን ነው?

**የአካል ጉዳተኞች ትምህርት ህግ (IDEA) በመላ አገሪቱ ውስጥ ብቁ ለሆኑ አካል ጉዳተኛ ልጆች አገልግሎትን የሚያረጋግጥ የፌደራል ህግ ነው።** የ IDEA ደንብ ስቴቶች እና የመንግስት ኤጀንሲዎች ከ 7.2 ሚሊዮን በላይ ብቁ ለሆኑ ህፃናት፣ ታዳጊዎች እና አካል ጉዳተኛ ልጆች እና ወጣቶች የቅድመ ጣልቃ ገብነት እና የልዩ ፍላጎት ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን እንዴት እንደሚያቀርቡ ይቆጣጠራል። የ Maryland ግዛት ከተወለዱበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 21 ዓመት ዕድሜ ድረስ አካል ጉዳተኛ ለሆኑ ህጻናት እንከን የለሽ፣ ሁሉን አቀፍ የተቀናጀ አገልግሎት ይሰጣል።

# **የልዩ ፍላጎት ትምህርት** ምንድን ነው?

**የልዩ ፍላጎት ትምህርት የልጅዎን ልዩ ፍላጎቶች ለማሟላት በልዩ ሁኔታ የተዘጋጀ የትምህርት አሰጣጥ ነው።** የልዩ ፍላጎት ትምህርት ቦታ ወይም ክፍል ሳይሆን አገልግሎት ነው። እንደ የንግግር ሕክምና፣ የምክር አገልግሎት ወይም የአካል ሕክምና ያሉ ተዛማጅ አገልግሎቶችን ሊያካትት ይችላል። ለቤተሰቡ ያለምንም ወጪ የሚቀርብ ሲሆን በተለያየ ጊዜና ቦታ ሊሰጥ ይችላል። የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት የሚቀበል ማንኛውም ልጅ ነፃ ተገቢ የሕዝብ ትምህርት (Free Appropriate Public Education) ወይም FAPE የማግኘት መብት አለው። ይህ ማለት ለልጅዎ አገልግሎቶች በነጻ ይሰጣሉ ማለት ነው። አገልግሎቶቹ በልጅዎ ልዩ ፍላጎቶች ላይ የተመሰረቱ ይሆናሉ። ዓላማው ልጅዎ በትምህርት ቤት ጥሩ ውጤት እንዲያመጣ እና ከትምህርት ቤት በኋላ ለሚኖረው ሕይወት ዝግጁ እንዲሆን ማድረግ ነው።

# ልጆችን **ማግኘት**

የ Maryland ትምህርት ቤቶች ስርዓቶች ወይም የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲዎች (LEAs) የልዩ ፍላጎት ትምህርት የሚያስፈልጋቸውን ከልደት እስከ 21 ዓመት ዕድሜ ያላቸውን ልጆች መፈለግ፣ መለየት እና መገምገም አለባቸው። ይህ የሚከተሉትን ልጆች ያጠቃልላል፦

- በቤት ውስጥ የሚማሩ፤
- በግል ትምህርት ቤቶች የሚማሩ፤
- ቤት የሌላቸውን፤
- ስደተኛ ወይም ከፍተኛ ተንቀሳቃሽነት ያላቸው፤
- በመንግስት ጥበቃ ስር ያሉ፤ ወይም
- ከክፍል ወደ ክፍል እየተሸጋገሩ ቢሆንም በአካል ጉዳተኝነት የተጠረጠሩ።

**የወላጅ(ዎች) ሚና፦**
በእርስዎ የትምህርት ቤት ስርዓት ውስጥ ያለውን የልዩ ፍላጎት ትምህርት አስተዳዳሪ ወይም የልጅ ማግኘት ቢሮን ወይም ልጅዎ በሕዝብ ትምህርት ቤት ውስጥ ያልተመዘገበ ከሆነ LEAን ያነጋግሩ። ልጅዎ በሕዝብ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማር ከሆነ፤ የትምህርት ቤቱን ርዕሰ መምህር ወይም የልጅዎን አስተማሪ ማነጋገር ይችላሉ።

# የ Maryland IEP ሂደት
# ወላጆች በእያንዳንዱ እርምጃ ላይ ድርሻ አላቸው

### ሪፈራል/ማጣራት

ልጅዎ አካል ጉዳተኛ ሊሆን ይችላል ብለው ካሰቡ ስለ ስጋቶችዎ ለመወያየት የግለሰባዊ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን ስብሰባ እንዲደረግ መጠየቅ አለብዎት። ጥያቄውን ለት/ቤቱ ርዕሰ መምህር ወይም ለአስተማሪው በጽሑፍ ማቅረቡ የተሻለ ነው። አስተማሪዎችም የሚያሳስባቸው ነገር ካለ ሪፈራል ሊያደርጉ ይችላሉ።

ትምህርት ቤቱ ስለ ስጋቶችዎ ለመወያየት እና ያለውን መረጃ ለመገምገም ለስብሰባ ይጋብዝዎታል። ቡድኑ የክፍል አፈጻጸም መረጃን፣ የስቴት ምዘናዎችን፣ የካውንቲ ግምገማ ውጤቶችን፣ በእርስዎ የቀረበውን መረጃ እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን ይገመግማል።

የዚህ ስብሰባ ውጤቶች የሚከተሉት ሊሆኑ ይችላሉ፦ (1) የትምህርት እክል ጥርጣሬዎች የሉም፤ ምንም እርምጃ አያስፈልግም፤ (2) የትምህርት እክል እንዳለ አሁን ላይ ምንም ጥርጣሬዎች የሉም፣ መደበኛ ወይም መደበኛ ያልሆኑ ጣልቃ ገብ እርምጃዎችን መተግበር እና በተወሰነ ጊዜ ውስጥ መረጃውን መከለስ፤ (3) የትምህርት እክል እንዳለ ጥርጣሬ አለ እና ተጨማሪ መረጃ ያስፈልጋል፤ ወይም (4) የትምህርት እክል መኖሩን ለመወሰን በቂ መረጃ አለ።

የስብሰባው ውጤት ምንም ይሁን ምን፣ ከስብሰባው በኋላ እና ማንኛውም ምክረ ሃሳቦች ከመተግበራቸው በፊት የቅድሚያ የጽሑፍ ማስታወቂያ (PWN) የሚባል የጽሑፍ ማብራሪያ ይደርስዎታል። ከዚህም በተጨማሪ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ መብቶችዎን እንዲያውቁ የሚያስችልዎ የእርስዎ የሥርዓት ከለላዎች የሚባል ሰነድ ይደርሰዎታል።

### የ IEP ሂደት




**የወላጅ(ዎች) ሚና፦**
በ IEP ስብሰባ ላይ መገኘት ካልቻሉ ተለዋጭ ቀጠሮ እንዲይዙ በተቻለ ፍጥነት ለት/ቤቱ ይንገሩ። በስብሰባ ግብዣው ላይ የመገናኛ መረጃ ይኖራል። በስብሰባው ላይ ስጋቶችዎን እና ከዶክተሮች ወይም መረጃ ከሰጡዎት ሌሎች ሰዎች የተገኙ ማንኛውንም ሪፖርቶች ያካፍሉ።

# የስብሰባ ግብዣ

**ከማንኛውም የ IEP ስብሰባ ቢያንስ 10 ቀናት በፊት ግብዣ ይደርስዎታል። ይህም የስብሰባውን ዓላማ፣ ሌሎች የተጋበዙት እነማን እንደሆኑና የስራ ድርሻ ወይም የስራ መደባቸው ይነግርዎታል።** እንዲሁም የስብሰባውን ሰዓት፣ ቀን እና ቦታም ያካትታል። ስብሰባዎች በጋራ ሊዘጋጁ ይገባል።

በተጨማሪም ከስብሰባው ቢያንስ 5 ቀናት በፊት በስብሰባው ላይ ውይይት የሚደረግባቸውን ማንኛውንም ሰነዶች ቅጂ ያገኛሉ።

በስብሰባው ላይ መገኘት ካልቻሉ እና ለሌላ ጊዜ እንዲተላለፍ ከፈለጉ በተቻለ ፍጥነት ለትምህርት ቤቱ ያሳውቁ። በአካል መገኘት ካልቻሉ በቨርቹዋል ወይም በስልክ ለመሳተፍ መምረጥ ይችላሉ።

# የ IEP ቡድን

**የ IEP ቡድን ዋና አባላት የሚከተሉትን ያካትታሉ፦**

- ወላጆች፤
- የልጁ አጠቃላይ ትምህርት መምህር፤
- የልጁ የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህር፤
- አስተዳዳሪ ወይም ተወካይ፤
- የምዘና ውጤቶችን መተርጎም የሚችል ገምጋሚ፤
- ተማሪው፣ አስፈላጊ ከሆነ፤ እና
- በወላጆች ወይም በአካባቢ ትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ወይም በሕዝብ ኤጀንሲ (PA) የተጋበዙ ስለ ተማሪው እውቀት ያላቸው ሌሎች ግለሰቦች።

የተማሪው አጠቃላይ አስተማሪ ከሌለ፣ ልጁ አካል ጉዳተኛ ካልሆኑ እኩዮች ጋር የመካተት እድሉ ካለው፣ አንድ የክፍል ደረጃ አስተማሪ ይሳተፋል።

## ግምገማ እና ምዘና

የትምህርት እክል መኖሩን ለመወሰን ተጨማሪ መረጃ ካስፈለገ ቡድኑ በሁሉም የተጠረጠሩ ተፅዕኖዎች ላይ ግምገማዎችን ይመክራል። የትምህርት ቤት ሰራተኞች የልጅዎን ፍላጎቶች እና ጥንካሬዎች ለመረዳት የተለያዩ ዓይነት ግምገማዎችን እና የመረጃ አሰባሰብ ስልቶችን ይጠቀማሉ።

ቡድኑ የሚከተሉትን ይመለከታል፦

- ነባር መረጃዎች እና የምዘና ውጤቶች፤
- ከእርስዎ፣ ከወላጅ (ዎች) የተገኘ መረጃ፤
- የክፍል፣ የስቴት አቀፍ እና በዲስትሪክት ደረጃ የሚደረጉ ምዘናዎች፤
- የክፍል ውስጥ ምልከታዎች፤ እና
- ከመምህራን የሚገኝ መረጃ።

**የወላጅ(ዎች) ሚና፦**
የዳሰሳ ጥናቶችን፣ የማረጋገጫ ዝርዝ
ሮችን ወይም ሌሎች ሰነዶችን እንዲሞሉ ሊጠየቁ ይችላሉ። ሞልተው በተቻለ ፍጥነት መልሰው ይላኳቸው።
አስፈላጊ ከሆነ ጥያቄዎችን ይጠይቁ፣ እንዲሁም መመሪያዎቹን ይከተሉ።

በሁሉም አሳሳቢ ጉዳዮች ላይ ይገመገማሉ። ይህ ማህበራዊ ስሜታዊ እና ባህሪን፣ ትምህርትን፣ አጠቃላይ የግንዛቤ ሙከራን፣ ንግግር እና ቋንቋ እና የሞተር ክህሎቶችን ሊያካትት ይችላል። የተሰበሰበው መረጃ ልጅዎ አገልግሎቶችን ለማግኘት ብቁ ከሆነ ማድረግ የሚችለውን ነገር ለመወሰን ለመነሻነት ይረዳል።

ለምዘናዎች የጽሑፍ ስምምነት ከደረሳቸው በኋላ በ60 ቀናት ውስጥ ውጤቱን ለመገምገም እና የልጅዎን የአገልግሎት ብቁነት ለመወሰን ሌላ ስብሰባ ይደረጋል። ከስብሰባው ቢያንስ 5 ቀናት በፊት ሁሉንም የምዘና ውጤቶች እና ውይይት የሚደረግባቸውን ማንኛውም ሰነዶች ቅጂ ያገኛሉ።

## በግምገማው ካልተስማማሁስ?

በግምገማው ውጤቶች ካልተስማሙ፣ በሕዝብ ወጪ የሚደረግ ገለልተኛ የትምህርት ግምገማ (IEE) እንዲደረግ፣ ወይም አለመግባባቱን ለመፍታት ሽምግልና ወይም የፍትህ ሂደት ችሎት መጠየቅ ይችላሉ።

IEE ከትምህርት ቤት ስርዓት ውጭ በሆነ ሰው የሚጠናቀቅ ግምገማ ነው። ትምህርት ቤቱ በገንዘብ ድጋፍ ጥያቄዎ ይስማማል ወይም አይሆንም ይላል እናም ጥያቄው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ጉዳዩን ለፍትህ ሂደት ችሎት ያቀርባል። በተጨማሪም በራስዎ ወጪ IEE ማግኘት ይችላሉ። የIEP ቡድን ስለልጅዎ ትምህርታዊ ውሳኔዎችን በሚያደርግበት ጊዜ ሁሉንም የውጭ ግምገማዎች ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት። አለመግባባቶችን ለመፍታት ስለሚያስችሏችሁ አማራጮች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በዚህ ተከታታይ ርዕስ ውስጥ የሚገኘውን የወላጅ መብት የተባለውን ቡክሌት ይመልከቱ።





## ለልዩ ፍላጎት ትምህርት ብቁ ለመሆን ያሉት የአካል ጉዳተኛነት ምድቦች ምንድናቸው?

- ኦቲዝም
- መስማት የተሳናቸው-ዓይነ ስውርነት
- የእድገት መዘግየት
- ስሜታዊ እክል
- የመስማት ችግር መስማት አለመቻልን ጨምሮ
- አዕምሯዊ እክል
- በርካታ የአካል ጉዳቶች
- ኦርቶፔዲክ እክል
- ሌሎች የጤና እክሎች
- የተወሰነ የመማር እክል
- የንግግር ቋንቋ እክል
- በአደጋ የተፈጠረ የአንጎል ጉዳት
- የማየት ችግር

---

## የ IEP ትግበራ

አንድ IEP ልክ እንደ ኮንትራት ነው። ውሎች መከበር አለባቸው፣ ስለዚህ በግልጽ መረዳት ያስፈልጋል። ቡድኑ እያንዳንዱ የIEP ክፍል በግልጽ የተብራራ መሆኑን እና እያንዳንዱ የቡድን አባል ተመሳሳይ ግንዛቤ እንዳለው ማረጋገጡ ወሳኝ ነው። ጥያቄዎችን ይጠይቁ፣ ሁሉም ሰው ተመሳሳይ ግንዛቤ እንዲኖረው በ IEP ሰነዱ ላይ ነገሮች ግልጽ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

IEP ከተጠናቀቀ በኋላ አገልግሎቶቹ እና ድጋፎቹ በተቻለ ፍጥነት ይጀመራሉ፣ ነገር ግን ይህ የሚሆነው በቡድኑ የቀረቡትን ሃሳቦች ለመገምገም እና ለማጤን ምክንያታዊ ጊዜ ካገኙ በኋላ ነው።

የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ከልጅዎ ጋር በመሆን በግቦቻቸው እና አላማዎቻቸው ላይ ይሰራሉ። ሁሉም የልጅዎ መምህራን በክፍል ውስጥ ሊጠቀሙባቸው የሚገቡ ማናቸውም ማስተካከያዎችን ጨምሮ በ IEP ውስጥ ያለው መረጃ ይሰጣቸዋል። የትምህርት ቤት ሰራተኞች ግቦች እና አላማዎችን በማሳካት ረገድ ያለውን መሻሻል በተመለከተ መረጃ ይሰበስባሉ።

በየሩብ ዓመቱ ወይም በ IEP ላይ እንደተገለጸው የሂደት ሪፖርቶችን ያገኛሉ። ልጅዎ መሻሻል እያሳየ ካልሆነ፣ በ IEP ላይ ምን ዓይነት ለውጦች ማድረግ እንደሚያስፈልግ ለመወያየት የ IEP ስብሰባ መኖር አለበት። ልጅዎ ተጨማሪ ወይም የተለዩ ድጋፎችን ሊፈልግ ወይም ግቦች መስተካከል ሊኖርባቸው ይችላል።

**የወላጅ(ዎች) ሚና:-**
ልጅዎን ለመርዳት በቤት ውስጥ ምን ማድረግ እንደሚችሉ የትምህርት ቤት ሰራ ተኞችን ይጠይቁ። ስጋቶችን እና አበረታች ለውጦችን ለአስተማሪዎች ያካፍሉ። አዲስ መረጃ ካለዎት፣ ስጋቶች ካሉዎት ወይም ልጅዎ መሻሻል እያሳየ ካልሆነ ስብሰባ እን ዲደረግ ይጠይቁ።

## የ IEP ዓመታዊ ግምገማ

የ IEP ቡድን የልጅዎን እድገት ለመገምገም እና IEPን ለመከለስ  ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ መገናኘት አለበት። ልጅዎ ከክፍል ወደ ክፍል ሲሸጋገር የ IEP ፕሮግራሙ ፍላጎቶቹን ማሟላት እንደሚቀጥል ለማረጋገጥ ይህ አስፈላጊ ነው። ወላጆች ወይም አስተማሪዎች ስብሰባ ከጠየቁ የ IEP ስብሰባዎች በተደጋጋሚ ሊደረጉ ይችላሉ።

በስብሰባው ላይ ውይይት የሚደረግባቸው ሁሉም ሰነዶች ከ IEP ስብሰባ 5 ቀናት በፊት ወደ ቤት ይላካሉ። ሰነዶች ከስብሰባው 5 ቀናት በፊት ካልተላኩ ሰነዶቹን የመገምገም እድል እስኪያገኙ ድረስ ለሌላ ጊዜ እንዲተላለፍ መጠየቅ ይችላሉ። ረቂቅ IEP ወደ ቤት ሊላክ ይችላል። ረቂቅ IEP የውይይት መነሻ እንደሆነ ልብ ይበሉ። ወደ ቤት የሚላኩት ረቂቆች ሁልጊዜ በስብሰባው ወቅት ሊለወጡ ይችላሉ።

ወደ ቤት የተላኩትን ሰነዶች መከለስዎ አስፈላጊ ነው፣ ያለዎትን ማንኛውም ጥያቄ በማስታወሻ ይያዙ።  በቤት ውስጥ ወይም ልጅዎ በትምህርት ቤት ስኬታማ እንዲሆን በሚረዱ ሌሎች እንቅስቃሴዎች ወቅት ለልጅዎ የሚጠቅሙ ነገሮችን ለማካፈል ዝግጁ ይሁኑ። ጥያቄዎችዎን ወይም ምክረ ሃሳቦችን ከስብሰባው በፊት ለልጅዎ ጉዳይ አስተዳዳሪ መላክ ይችላሉ ይህም ቡድኑ ለጥያቄዎቹ ምላሽ ለመስጠት ዝግጁ እንዲሆን ያደርጋል።

**የወላጅ(ዎች) ሚና፦**
በስብሰባው ላይ መገኘት ካልቻሉ ሌላ ቀጠሮ ያስይዙ። ስጋቶችን እና ስኬቶችን ለቡድኑ ያካፍሉ። ከትምህርት ቤት ወይም ከቤት ስራ ወዘተ… ጋር በተገናኘ ቤት ውስጥ ስላስተዋሉት ነገር ይናገሩ። ግብረመልስ ይስጡ እና ለለውጦች አስተያየት ይስጡ።
ከስብሰባው በፊት እና በኋላ ወደ ቤት የተላኩትን ሰነዶች በሙሉ ይከልሱ።

ቡድኑ በሚያቀርባቸው የመጨረሻ ምክሮችን በተመለከተ ሊኖሩዎት የሚችሉ የማሻሻያ እና ማብራሪያ አስተያየትዎን ለቡድኑ ማካፈልዎን ወይም አለመግባባቶችን መግለጽዎን ያረጋግጡ። የ IEP ቡድን  እኩል እና በጣም ጠቃሚ አባል ነዎት። የእርስዎ ድምጽ እና ጥያቄዎች ለቡድኑ እና ለሂደቱ አስፈላጊ ናቸው።

---

## ዳግም ግምገማ

**የወላጅ(ዎች) ሚና፦**
ማንኛውንም አዲስ መረጃ እና ስጋቶችን ለተቀሩት የቡድኑ አባላት ያካፍሉ። የዳግም ግምገማው አካል ሆኖ ወደ ቤት የተላኩትን ማንኛውንም ሰነዶች፣ የማረጋገጫ ዝርዝሮች፣ ወዘተ አጠናቅቀው ይመልሱ። በሁሉም ስብሰባዎች ላይ ይሳተፉ። ሃሳብዎን ይስጡ፣ ስጋቶችዎን እና አስተያየቶችዎን ያካፍሉ።

ቢያንስ በየ 3 ዓመቱ የ IEP ቡድን ልጅዎ አሁንም ለልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት ብቁ መሆኑን መወሰን አለበት። እንዲሁም ስለልጅዎ ፍላጎቶች እና ጥንካሬዎች ወቅታዊ መረጃ እንዳላቸው ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል። ወላጆች እና የትምህርት ቤት ሰራተኞች ስጋቶች ካሉ ወይም አዲስ መረጃ ካስፈለገ ምዘና ቀደም ብሎ እንዲደረግ መጠየቅ ይችላሉ።

የIEP ቡድን የልጅዎን አገልግሎት የማግኘት ብቁነት ቀጣይነት ለማረጋገጥ ወይም አሁን ያለውን የአፈጻጸም ደረጃ ለመወሰን ምንም ተጨማሪ መረጃ አያስፈልግም ብሎ ሊወስን ይችላል። ቡድኑ ተጨማሪ ምዘናዎች አስፈላጊ እንደሆኑ ሊወስን ይችላል። ይህ ከሆነ በውጤቶቹ ላይ ለመወያየት እና አስፈላጊ ከሆነም IEPን ለማሻሻል ምዘናዎቹ እንዲጠናቀቁ ፈቃድ ከሰጡ በኋላ በ90 ቀናት ውስጥ እንደገና ይሰበሰባሉ።

ልጅዎ ከልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ከመሰናበቱ በፊት ልጅዎ በድጋሚ መገምገም አለበት። ቡድኑ ልጅዎን ለማሰናበት ምንም ተጨማሪ መረጃ እንደማያስፈልግ ከወሰነ፣ ከመሰናበቱ በፊት ምዘናዎች እንዲደረጉ የመጠየቅ መብት አለዎት።



# **ለወላጆች** የማረጋገጫ ዝርዝር

## ከስብሰባው በፊት

❍ ለስብሰባ ለቀረበው ግብዣ ምላሽ ይስጡ።

❍ ወደ ቤት የተላኩትን ሰነዶች በሙሉ ይከልሱ።

❍ ለልጅዎ የእርስዎን ራዕይ ይፍጠሩ ወይም ያዘምኑ።

❍ በስብሰባው ላይ ለማጋራት የሚፈልጉትን ማንኛውንም ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ይጻፉ።

❍ የወላጅ አስተያየትዎን ያዘጋጁ (ከስብሰባው በፊት መላክ ይችላሉ)።

❍ የሚያስፈልግዎት ከሆነ፣ አስተርጓሚ ይጠይቁ።

## በስብሰባው ወቅት

❍ እድሜው ምንም ይሁን ምን ልጅዎ በስብሰባው ላይ እንዲሳተፍ ያስቡበት። ይህ በራስ የመደገፍ ክህሎትን ያዳብራል እንዲሁም ቡድኑ ልጅዎን በተሻለ ሁኔታ እንዲረዳ ያግዛል። ዕድሜያቸው 14 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ተማሪዎች ወደ IEP ስብሰባዎቻቸው መጋበዝ አለባቸው።

❍ የእርስዎን ራዕይ እና ግብአት ለቡድኑ ያካፍሉ።

❍ ጥያቄዎችን ይጠይቁ እንዲሁም ሀሳብዎን ያካፍሉ።

## ከስብሰባው በኋላ

❍ ከስብሰባው በኋላ የተላኩትን ሁሉንም ሰነዶች ይመልከቱ።

❍ ሰነዶች በ5 ቀናት ውስጥ ካልደረሱዎት ወይም ወደ ቤት ስለተላኩ ሰነዶች ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካሉዎት የ IEP ሰብሳቢን ወይም የልጅዎን መምህር ያነጋግሩ።

❍ ልጅዎ የትምህርት ቤትና የቤት ሥራዎቹን እንዴት እያከናወነ እንደሆነ ይከታተሉ።

❍ ማንኛውንም ስጋት ለልጅዎ አስተማሪ ያካፍሉ።

❍ አስፈላጊ ከሆነ የ IEP ስብሰባ ይጠይቁ። ይህንን በጽሑፍ ወይም በኢሜይል ማድረጉ የተሻለ ነው።

# የቃላት መፍቻ

**ምዘና**
የግምገማው አካል በመሆን በሁሉም አሳሳቢ ጉዳዮች ላይ የሚሰጡ የተወሰኑ ምዘናዎች። የልጅዎን ጥንካሬዎች እና ፍላጎቶች ለመለየት ይረዳሉ።

**ልጆችን ማግኘት**
የልዩ ፍላጎት ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚያስፈልጋቸውን የአካል ጉዳተኛ ልጆችን ለመለየት፣ ለማግኘት እና ለመገምገም በስቴቶች እና በአከባቢያዊ የስልጣን ወሰኖች ውስጥ በህግ እንዲከናወኑ የሚጠየቁ ተግባራት።

**ስምምነት**
ለታቀዱት እርምጃዎች የጽሑፍ ስምምነት።

**ግምገማ**
ልጆች የአካል ጉዳት እንዳለባቸው እና የልዩ ፍላጎት ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች እንደሚያስፈልጋቸው ለመወሰን፤ ከወላጆች፣ ከነባር የመማሪያ ክፍል መረጃዎች፣ የምዘና ውጤቶች፣ ወዘተ የተገኙ መረጃዎችን የመገምገም ሂደት።

**FAPE**
የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት የሚቀበል ማንኛውም ልጅ ነፃ ተገቢ የሕዝብ ትምህርት (Free Appropriate Public Education) (FAPE) የማግኘት መብት አለው።

**IDEA**
የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ህግ። ይህ የአገሪቱ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ሕግ ነው።

**IEP**
የግለሰባዊ ትምህርት መርሃ ግብር (The Individualized Education Program፣IEP) ይህ በ IEP ቡድን የተዘጋጀ ሰነድ ነው። ለልጅዎ የሚሰጡትን አገልግሎቶች፣ ድጋፎች እና ልዩ የትምህርት አሰጣጥ ይገልጻል። እያንዳንዱ ልጅ በሚያስፈልገው ነገር ላይ ተመሥርቶ IEP ይዘጋጃል።

**የ IEP ቡድን**
የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ለሚያስፈልገው ልጅ ውሳኔዎችን የሚሰጡ ሰዎች ቡድን። ወላጆች አስፈላጊ የ IEP ቡድን አባላት ናቸው።

**LRE**
አነስተኛ ገዳቢ አካባቢ የልጅዎ IEP የሚሟላበት ቦታ። በአጠቃላይ ትምህርት ቤቶች በተቻለ መጠን የአካል ጉዳተኛ ልጆችን የአካል ጉዳተኛ ካልሆኑ እኩዮቻቸው ጋር ማስተማር ይጠበቅባቸዋል።

**ወላጅ**
የተፈጥሮ ወይም የጉዲፈቻ፣ ወላጅ፣ ሞግዚት፣ ተጠሪ ወላጅ ወይም ምትክ ወላጅ፤ ልጁ በስቴት ጥበቃ ስር ከሆነ ይህ ቃል ስቴቱን አያካትትም።

**ምደባ**
ልጅዎ የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቱን የሚያገኝበት ቦታ። ምደባ የሚወሰነው ግቦቹ እና አገልግሎቶቹ ከተፃፉ በኋላ ነው።



# **ከልዩ ፍላጎት ትምህርት ሂደት** ጋር የተያያዙ የጊዜ ሰሌዳዎች

| ምን | መቼ |
|---|---|
| ወላጅ የ IEP ስብሰባ ግብዣ መቀበል አለባቸው | ከ IEP ስብሰባ **10 የቀን መቁጠሪያ ቀናት በፊት** |
| ወላጆች በ IEP ስብሰባ ላይ የሚገመገሙ ሰነዶችን መቀበል አለባቸው | ከ IEP ስብሰባ **5 የስራ ቀናት በፊት** |
| ወላጆች የተጠናቀቀ IEP ወይም ካልተጠናቀቀ የ IEP ረቂቅ ቅጂ መቀበል አለባቸው | ከ IEP ስብሰባ **5 የስራ ቀናት በኋላ** |
| ብቁነትን ለመወሰን ግምገማዎችን ለመወያየት ስብሰባ መደረግ አለበት | የጽሑፍ ስምምነት ከሰጡ በኋላ **በ 60 ቀናት ውስጥ** |
| ልጅዎ ብቁ እነደሆነ ከተረጋገጠ በኋላ IEP መዘጋጀት አለበት | ልጅዎ ለልዩ ፍላጎት ትምህርት ብቁ እንደሆነ ከተረጋገጠ በኋላ **በ30 ቀናት ውስጥ** |
| IEP መተግበር አለበት | **በተቻለ ፍጥነት** |
| መሻሻል ሪፖርት መደረግ አለበት | **ቢያንስ በየሩብ ዓመቱ** እና በልጅዎ IEP ላይ እንደተገለጸው |
| IEP መገምገም እና መዘመን አለበት (የዓመታዊ ግምገማ ስብሰባ) | ቢያንስ **በዓመት አንድ ጊዜ** |
| የ IEP ቡድን የዳግም ግምገማዎችን አስፈላጊነት ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት | ቡድኑ ምንም አዲስ መረጃ አያስፈልግም ብሎ ካልወሰነ በስተ ቀር፣ ቢያንስ **በየ 3 ዓመቱ** |
| የዳግም ግምገማ ውጤቶች መከለስ አለባቸው እና አስፈላጊ ከሆነ IEP መከለስ አለበት | ለምዘናዎች የጽሑፍ ስምምነት ከሰጡ በኋላ **በ 90 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ** |
| ለገለልተኛ የትምህርት ግምገማ (IEE) ጥያቄ የትምህርት ቤቱ ስርዓት ምላሽ መስጠት አለበት | ጥያቄውን ከተቀበለ በኋላ **በ 30 የቀን መቁጠሪያ ቀናትውስጥ** |

# ጥያቄዎች ካሉኝ ወይም **እርዳታ ቢያስፈልገኝስ?**

## አካባቢያዊ የቤተሰብ ድጋፍ አገልግሎት አስተባባሪዎች

| የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲዎች | ዕድሜ ከልደት እስከ 5 ዓመት | ዕድሜ ከ 5 እስከ 21 ዓመት |
|---|---|---|
| **Allegany** | 240-920-6829 | 240-920-6829 |
| **Anne Arundel** | 410-562-6303 | 410-424-3258 |
| **Baltimore City** | 410-396-1666 | 443-642-3848 |
| **Baltimore County** | 443-809-9696 | 443-809-5443 |
| **Calvert** | 443-550-8406 | 443-550-8375 |
| **Caroline** | 410-479-3609 | 410-479-3609 |
| **Carroll** | 410-751-3955 | 410-751-3955 |
| **Cecil** | 410-996-5637 | 410-996-5637 |
| **Charles** | 301-934-7456 | 301-934-7456 |
| **Dorchester** | 410-901-6915 | 410-901-6915 |
| **Frederick** | 240-578-1244 | 240-236-8744 |
| **Garrett** | 301-533-0240, x2 | 301-914-1351 |
| **Harford** | 410-273-5579 | 410-273-5579 |
| **Howard** | 410-313-7161 | 410-313-7161 |
| **Kent** | 410-778-5708 | 410-778-5708 |
| **Montgomery** | 240-777-4809 | 240-753-9487 |
| **Prince George’s** | 240-521-5054 | 301-431-5675 |
| **Queen Anne’s** | 410-556-6103, x10 | 410-758-2403, x135 |
| **Somerset** | 410-651-1616, x11385 | 410-651-1616, x11385 |
| **St. Mary’s** | 301-475-5511, x32218 | 240-309-4113 |
| **Talbot** | 410-822-0330 | 410-822-0330 |
| **Washington** | 301-766-8221 | 301-766-8221 |
| **Wicomico** | 410-677-5250 | 410-677-5250 |
| **Worcester** | 410-632-5234 | 410-632-5234 |
| **የ Maryland አይነ ስውራን ትምህ ርት ቤት** | 410-444-5000, x1489 | |
| **የሜሪላንድ መስማት የተሳናቸው ትም ህርት ቤት** | 443-277-8899 | |
| **የ Maryland ስቴት የትምህርት መምሪያ** | 410-767-0255 | |

**የ MARYLAND ስቴት የትምህርት መምሪያ**

**Mohammed Choudhury**
የስቴቱ የትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ

**Dr. Deann Collins**
የማስተማር እና መማር ቢሮ ምክትል የበላይ ተቆጣጣሪ

**Clarence C. Crawford**
የ Maryland ስቴት የትምህርት ቦርድ፣ ፕሬዝዳንት

**Wes Moore**
አስተዳዳሪ

© 2023 የ Maryland ስቴት የትምህርት መምሪያ
ይህ ህትመት የተዘጋጀው በ Maryland ስቴት የትምህርት መምሪያ፤ የቅድመ ጣልቃ ገብነት ክፍል እና የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ከዩናይትድ ስቴትስ የትምህርት መምሪያ፤ የገንዘብ ድጋፍ #H393A090124A፤ የልዩ ፍላጎት ትምህርት የገንዘብ ድጋፍ ለህፃናት እና ቤተሰቦች “የማገገሚያ የገንዘብ ድጋፎች” በ PL 105-17/111-5 መሰረት የአካል ጉዳተኛ ግለሰቦች የትምህርት ህግ/የአሜሪካ ማገገሚያ እና መልሶ ማልማት ህግ በተገኘ ገንዘብ ድጋፍ ነው። የ Maryland ስቴት የትምህርት መምሪያ፤ የቅድሚያ ጣልቃገብነት ክፍል እና የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች፤ ለ Maryland ሕፃናት እና ታዳጊዎች መርሃ-ግብር መሪ ወኪል ድርጅት ነው፤ በስቴት እና በአካባቢ ኤጀንሲዎች እና ድርጅቶች የተቀናጁ የስቴት አቀፍ የአገልግሎት መርሃ-ግብሮች እና ድጋፎች። በዚህ ህትመት ውስጥ ያለውን መረጃ የሚያባዙ ወይም የሚያጋሩ ተጠቃሚዎች ለ Maryland ስቴት የትምህርት መምሪያ፣ የቅድመ ጣልቃ ገብነት እና የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ክፍል እውቅና መስጠት አለባቸው፣ Dr. Deann Collins፣ የማስተማር እና መማር ቢሮ ምክትል የበላይ ተቆጣጣሪ።



MARYLAND STATE DEPARTMENT OF
EDUCATION
EQUITY AND EXCELLENCE

410-767-0100

www.marylandpublicschools.org

200 West Baltimore Street
Baltimore, MD 21201-2595